ርዕስ: ተሳፋሪዎች ማወቅ ያለባቸው

ሲያትል እና ኪንግ ካውንቲ በተሽከርካሪ ወንበሮች ተደራሽ የሆኑ ተሽከርካሪዎች (WAVs) በጥያቄ የሚገኙ መጓጓዣ አላቸው። ተሽከርካሪ ወንበሮችን የሚጠቀሙ ተሳፋሪዎች በጥያቄ ወደ ሚገኝ በተሽከርካሪ ወንበሮች ተደራሽ የሆኑ ተሽከርካሪዎች (WAV) መጓጓዣ አገልግሎት አቅራቢ በመደወል እና ተሽከርካሪ ላኪውን በተሽከርካሪ ወንበሮች ተደራሽ የሆኑ ተሽከርካሪዎችን (WAV) እንፈልጋለን ብለው ነግረው ሊጠይቁ ይችላሉ። አንድ ዓይነት ዋጋ ያለው መጓጓዣ እና በታክሲዎች መካከል ስላለው ልዩነት መረጃ እዚህ ማግኘት ይቻላል።

በተሽከርካሪ ወንበሮች ተደራሽ የሆኑ ተሽከርካሪዎች (WAVs) ስላላቸው አቅራቢዎች የእውቂያ መረጃ በሚከተሉት ላይ ይገኛል:

| | | |
|---|---|---|
| ኢ-ካብ እና ፍላት ሬይት-ተመን ለ-ኪራይ (E-Cab & Flat-Rate For-Hire) | 206-242-8800 | |
| ፋርወስት (Farwest) ታክሲ | 206-622-1717 | www.farwesttaxi.net |
| ግሪን ካብ (Green Cab) | 206-575-4040 | www.greencab.me |
| የለው ካብ (Yellow Cab) | 206-622-6500 | www.seattleyellowcab.com |

በአሁኑ ወቅት፣ በሲያትል እና በኪንግ ካውንቲ ከ70 በላይ በተሽከርካሪ ወንበሮች ተደራሽ የሆኑ ተሽከርካሪዎች (WAVs) ይሰራሉ። ተሽከርካሪ ወንበሮችን ለሚጠቀሙ መንገደኞች የሚከፈለው ዋጋ ለሁሉም ከተለጠፈው ዋጋ ጋር ተመሳሳይ ነው።

የተሽከርካሪ ወንበር ተደራሽነት ያላቸው ተሽከርካሪዎች በፌዴራል ደንብ ቁጥር 49 CFR 38.23 ከተገለጹት የፌዴራል የተደራሽነት ደረጃዎች ጋር ይስማማሉ/ ይጣጣማሉ። የፌዴራል ደረጃዎች ማንሻው ወይም መወጣጫው 600 ፓውንድ ክብደት መደገፍ ያስፈልጋቸዋል፣ የበሩ ቁመት ቢያንስ 56 ኢንች ከፍ ያለ እና ከ1:4 (14.04 ዲግሪ) በታች የሆነ የመወጣጫ ቁልቁለት/ ዳገት መሆን አለበት።

አብዛኛዎቹ በሲያትል/ኪንግ ካውንቲ የሚገኙ የተሽከርካሪ ወንበሮች ተደራሽ ታክሲዎች Toyota Siennas እና Dodge Grand Caravans ናቸው። የደህንነት መሳሪያዎች ተሽከርካሪ ወንበሮችን በቦታቸው ይይዛሉ እና በተሽከርካሪ ወንበር ላይ የተቀመጠው ተሳፋሪ መንገደኛ በትክክል መታጠቂያ እና በጭን ቀበቶ ይጠበቃል። WATs አብዛኛውን የአዋቂ መጠን ያለው በእጅ የሚሰራ እና በሃይል የሚሰሩ ተሽከርካሪ ወንበሮችን ማስተናገድ ይችላል፤ ነገር ግን፣ እግራቸውን መዘርጋት የሚፈልጉ ወይም ጀርባቸዉን ማስጠጋት ወይም መንጋለል የሚፈልጉ ተሳፋሪዎች፣ ተሽከርካሪ ላኪውን ይህንኑ ጠቅሰው ማሳወቅ አለባቸው።

የተሽከርካሪ ወንበሮች ተደራሽ የሆኑ ታክሲዎች አሽከርካሪዎች ሁሉም አመታዊ የፈቃድ አሰጣጥ ፍተሻቸውን ለማለፍ የWAT የምስክር ወረቀት ስልጠና ማጠናቀቅ አለባቸው እና ተገቢውን የተሽከርካሪ ወንበሮች ደህንነት አሰራር ተሞክሮዎችንም ማሳየት አለባቸው። መሳሪያዎች የተደራሽነት ደረጃዎችን ማሟላታቸው እና በተነደፈው መልክ መስራታቸውን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል።

በተሽከርካሪ ወንበሮች ተደራሽ የሆኑ ተሽከርካሪዎች (WAV) የሥራ ፍቃድ እና የኢንሹራንስ ዋስትና ለመጓጓዣ ብቻ ነው። በተሽከርካሪ ወንበሮች ላይ የሚጓዙ ተሳፋሪዎች ለሌሎች የጉዞዋቸው ጉዳዮች እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ተጨማሪ ዝግጅቶችን ማድረግ ያስፈልጋቸው ይሆናል።

በተሽከርካሪ ወንበሮች ተደራሽ የሆኑ ተሽከርካሪዎች (WAV) ባለቤቶች እና አሽከርካሪዎች፣ የተሽከርካሪ ወንበሮች ተደራሽ መጓጓዣ ለማቅረብ ከፍተኛ የስራ ማስኬጃ ወጪዎችን ለማካካስ በተሽከርካሪ ወንበሮች የተደራሽነት አገልግሎት (WAS) የገንዘብ ድጋፍ በኩል ተመላሽ ሊያገኙ ይችላሉ። ይኸውም በሲያትል እና በኪንግ ካውንቲ በኪራይ በሚጓዙ ተሳፈሪዎች ላይ በአስር ሳንቲም ተጨማሪ ክፍያ ፈንድ ነው።

የሸማቾች የጥበቃ ክፍል የታክሲ አገልግሎት ለሁሉም ሰው ደህንነቱ የተጠበቀ ደስታን ለመስጠት ቁርጠኛ ነው። ከ WAV አሽከርካሪ ጋር ጥሩ ወይም መጥፎ ተሞክሮን ሪፖርት ለማድረግ፣ ወይም የተበላሹ መሳሪያዎችን ሪፖርት ማድረግ ከፈለጉ፣ እባክዎን 206.386.1267 ወይም consumerprotection@seattle.gov ያግኙ።